በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 1/1200/10
ቀን / Date 02 ጳጉሜ 2010

በዝርዝሩ ለተመለከቱት

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ መላክን ይመለከታል</u>

የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሠጣጥ መመሪያ ቁጥር 139/2010 ከዚህ ጋር ተያይዞ የተላከላችሁ ስለሆነ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

[illegible] ሁሴን አባ
ዋና ዳይሬክተር /ሚኒስትር



ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 [illegible]
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

- ለሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት
- ለኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት
- ለዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት
- ለፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጥናትና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለአገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት ልቀት ማዕከል ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አስተዳደር ማጣጣምና የክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለአምራቾችና የወጪ ንግድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲት አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተለጀንስ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለኮንትሮባንድ ክትትልና ዕቃ አወጋገድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥና የመልካም አስተዳደር ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሥልጠና ማዕከል ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለትምህርትና ሥልጠና ዳይሬክቶሬት
- ለሥልጠና ማስተባበርና ግብዓት አቅርቦት ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶት ም/ዳይሬክተር
- ለአገር ዉስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር
- ለኦዲት አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ም/ዳይሬክተር
- ለአቅም ግንባታና ሀብት አስተዳደር ዘርፍ ም/ዋ ዳ/ር ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለአገር ውስጥ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለጉምሩክ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት ኃላፊ
- ለህግ ማስከበር ዘርፍ ም/ዋና ዳ/ር ጽ/ቤት ኃላፊ

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ

## ቁጥር 139/2010

ነሐሴ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No.2

# የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር139/2010

በአዲሱ የፌደራል የታክስ አስተዳደር እና የገቢ ግብር አዋጅ የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች በአዋጆቹ የተካተተ ሲሆን ታክስ ከፋዩ በታክስ ሕግ መሠረት የተጣለበትን ታክስ የመክፈል ግዴታ የፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሰጣጥን በተመለከተ ለማስፈፀም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 61(2) በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## የወል ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል፡-

1. "የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት" ማለት አንድ ታክስ ከፋይ የታክስ ክፍያ ግዴታን መወጣቱን ወይም እየተወጣ መሆኑን የሚገልጽ ከታክስ ባለስልጣኑ በጹሁፍ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው፡
2. "ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ማለት ታክስ ከፋዩ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰዉ ሰራሽ ምክንያቶች የሚከሰቱ፤በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም የተፈጠረ ጦርነት፣ የመድን ሽፋን የሌላቸውና በንግድ ስራው ላይ ጫና የሚፈጥር (እንደ ዝርፊያ፣ ጉርፍ፣ቃጠሎ፣የመሬት መንቀጥቀጥ፣ መብረቅ፣ ተምች)፣ የታክስ ከፋዩ ጽኑ ህመም ወይም ሞት ሲያጋጥም፡ ወይም የታክስ እንደራሴ የሌለዉ ጽኑ ህመም ወይም ሞት ሲያጋጥም እና ታክስ ከፋዩ ያለበትን የግብር፣ ታክስ ወይም ቀረጥ የታክስ ዕዳ መክፈል አለመቻል ማለት ነው፡፡

3. **"ጽኑ ህመም"** ማለት በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ መስራት የማያስችልና በታወቀ የህክምና ተቋም የሚያስተኛ ህመም ላይ የነበረ መሆኑን በህክምና ማስረጃ የሚረጋገጥ ወይም የንግድ ስራ እንቅስቃሴውን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ መታመም ነው፡፡

4. **"የታክስ ዕዳ"** ማለት ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲሆን በታክስ ህግ መሰረት ለባለስልጣኑ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ ማንኛውንም የታክስ ከፋዩን ውዝፍ ታክስ ወይም ወለድ ወይም የታክስ አስተዳደር መቀጫዎችን እንዲሁም የጉምሩክ ቀረጥን ይጨምራል፡፡

5. **"የታክስ ቅሬታ የስራ ክፍል"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተቋቋመ የስራ ክፍል ነው፤

6. **"ከፍተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት ተቋሙ ባስቀመጠው ከፍተኛ የስጋት ወሰን ክልል (Range) ውስጥ ያረፈ ወይም በግብር ዘመኑ ኦዲት እንዲደረግ የተመረጠ ታክስ ከፋይ ሆኖ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የመፍጠር አቅም ያለው ማለት ነው፤

7. **"መካከለኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት ተቋሙ ባስቀመጠው መካከለኛ የስጋት ወሰን ክልል (Range) ውስጥ ያረፈ ታክስ ከፋይ ሆኖ መካከለኛ አሉታዊ ተጽዕኖና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የመፍጠር አቅም ያለው ማለት ነው፤

8. **"ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ"** ማለት በስጋት መምረጫ መስፈርት መሰረት ተቋሙ ባስቀመጠው ዝቅተኛ የስጋት ወሰን ክልል (Range) ውስጥ ያረፈ ታክስ ከፋይ ሆኖ ዝቅተኛ አሉታዊ ተጽዕኖና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የመፍጠር አቅም ያለው ማለት ነው፤

9. **"የታክስ ኦዲት"** ማለት ኦዲት የሚያስፈልገው የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አገልግሎት የጠየቀ ታክስ ከፋይ የሒሳብ መግለጫና ደጋፊ ሰነዶች እንዲያቀርቡ በማድረግ መከፈል የሚገባው ያልተከፈለ ታክስ ስለመኖሩ ዝርዝር የሒሳብ ምርመራ በመስራት ለማረጋገጥ የሚተገበር ስርዓት ነው፡፡

10. **"ዴስክ ኦዲት"** ማለት የሰነድ ማረጋገጫ የሚያስፈልገው የክሊራንስ አገልግሎት የጠየቀ ታክስ ከፋይ በታክስ ባለስልጣኑ የሚገኝ መረጃ እና እንደአስፈላጊነቱ

ከሶስተኛ ወገን ከሚገኙ መረጃዎች ጋር በማመሳከር መከፈል የሚገባው ያልተከፈለ ታክስ ስለመኖሩ በሂሳብ ምርመራ ለማረጋገጥ የሚተገበር ስርዓት ነው፡፡

11. **"የንግድ ሥራ ሀብት"** ማለት የንግድ ሥራ በማከናወን ሂደት በሙሉ ወይም በከፊል የንግድ ሥራ ገቢ ለማግኘት የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የዋለ ሀብት ነው፡፡
12. **"አዋጅ"** ማለት የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡
13. **"ባለሥልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ሲሆን የባለሥልጣኑን ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲሁም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለስልጣንን ይጨምራል፡፡
14. በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ፣በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ እና በሌሎች የታክስ ህጎች የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት በሚጠይቁ የታክስ ክፍያ ግዴታቸውን በተወጡ ወይም በመወጣት ላይ ባሉ ታክስ ከፋዮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የአገልግሎት አይነቶችና መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

### 4. የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች፤

ባለስልጣኑ ታክስ የመክፈል ግዴታውን ለተወጣና በመወጣት ላይ በሚገኝ ታክስ ከፋይ በሚቀርብ ጥያቄ መነሻነት ቀጥሎ በተዘረዘሩት አገልግሎቶችና ሌሎች መሰል አገልግሎቶች በዚህ መመሪያ መሰረት ተጣርቶና ተረጋግጦ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

1. የንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ ለማደስ፣
2. በጨረታ ለመካፈል ወይም ለመሳተፍ፣

Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No.2

3. ለተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ /ክላውዶ/ ለማድረግ፣
4. የባንክ ብድር ለማግኘት፣
5. ተሽከርካሪ ለመሸጥ ወይም ስም ለማዛወር ወይም የመድን ካሣ ለማግኘትና የሰሌዳ ለውጥ ለማድረግ፣
6. የድርጅት ስም ወይም አድራሻ ለመለወጥ፤
7. ጥቅም የሚከፈልበት የካፒታል ሃብት ለማስተላለፍ፣
8. ድርጅት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት ወይም ዘርፍ ለመቀየር፣
9. የባለቤትነት ስም ምዝገባ የሚያስፈልጋቸው የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፣
10. ህጋዊ ህልውና የነበራቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለማዋሀድ፣
11. በንግድ ስራ የተሰማራ ግለሰብ ወይም ድርጅት የመኖሪያና የንግድ ቤት ለመሸጥ ወይም የንግድ መደብር ለሌላ አካል በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስ ወይም የአክሲዮን ባለቤትነት መብት ለማዛወር ወይም በመሳሰሉት ለማስተላለፍ፣
12. ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ግብርን ስለመክፈሉ ለተቀጣሪው የሚሰጥ ማረጋገጫ፣
13. የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ተጠቃሚ በትምህርት ዘመኑ የተጋራውን ወጪ በአገልግሎት ወይም በክፍያ ስለመወጣቱ የሚሰጥ ማረጋገጫ፣
14. ለውጪ ንግድ ስርዓት ተጠቃሚዎች የቫውቸር እድሳት ለማድረግ፤ እና
15. ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ለማግኘት፡፡

## 5. የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

1. ማንኛውም ታክስ ከፋይ የታክስ ክሊራንስ ጥያቄ ሲያቀርብ የምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ድንጋጌዎች መሰረት ለማጣራትና ለማረጋገጥ በቅድሚያ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው መረጋገጥ አለበት፡፡

ሀ. የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው በጽሑፍ ጥያቄ ማቅረብ፤

ለ. ከታክስ ከፋዩ የሚፈለግ ማንኛውንም ወርሃዊ ወይም አመታዊ የታክስ ማስታወቂያ በወቅቱ መቅረቡንና የሚፈለግበትን ማንኛውንም የታክስ ዕዳ ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣ወይም

ሐ.ውዝፍ የታክስ ዕዳ ወይም ወቅታዊ የታክስ ዕዳ ለመክፈል የክፍያ ስምምነት የገባና በውሉ መሠረት እየተከፈለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ መቅረቡን፤ ወይም

መ.ታክስ ከፋዩ በደረሰው የታክስ ዉሳኔ ማስታወቂያ ላይ ቅሬታ ካለዉ ለታክስ ቅሬታ ስራ ክፍል ወይም ለግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ለሚገኝ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመታየት ላይ ስለመሆኑ የጽሁፍ ማስረጃ መቅረቡን፤ ወይም

ሠ.ታክስ ከፋዩ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት የታክስ ወይም የቀረጥ ግዴታውን አለመወጣቱ ተረጋግጦ በሚመለከተው አካል የተወሰነ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መቅረቡን ማጣራት ይኖርበታል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ቢኖርም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሳይሟሉና ሳይረጋገጡ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት አይቻልም፡፡

ሀ. ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ በማስቀረት ለባለስልጣኑ ገቢ መደረግ ያለበትን ሳይጨምር፣ ታክስ ከፋዩ ከታክስ ነፃ መብት ወይም የግብር እፎይታ ጊዜ ላይ ለሆነ ዘርፍ ከሚመለከተዉ አካል የተሰጠ የጽሁፍ ማስረጃ እስኪቀርብና እስኪረጋገጥ ድረስ፣ወይም

ለ. ታክስ ከፋዩ ለቀደመው አመት ወይም ለቀደሙት አመታት በታክስ ከፋይነት ያልተመዘገበ ወይም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አለመዉሰዱ እና የግብር ፋይል አለመክፈቱ እስኪረጋገጥ፣ወይም

ሐ. ታክስ ከፋዩ ባመለከተበት የግብር ዘመን የተመዘገበ ሆኖ በንግድ ሥራ ፈቃዱ ምንም ዓይነት ሥራ አለመስራቱን የገለጸ ታክስ ከፋይ አለመስራቱ እስኪረጋገጥ፣ወይም

መ. በኮንስትራክሽን ማሽነሪ ማከራየት ዘርፍ የተሰማራ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ ግብር ያልከፈለው ማሽነሪው በመበላሸቱ ምክንያት አለመስራቱን

በታክስ ህጉ መሠረት ማስታወቁን እና ይህንን የሚያረጋግጥ በ3ኛ ወገን የተረጋገጠ ማስረጃ እስኪቀርብ፣

ሠ. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) አፈጻጸም ለፊቃድና ቦሎ ማደሻ ታክስ ከፋዩ የኮንስትራክሽን ማሽን በመበላሸቱ ምክንያት ያለመስራቱን በ30 ቀናት ውስጥ ካስታወቀ፣ ወይም

ረ. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (መ) አፈጻጸም በኮንስትራክሽን ማሽነሪ ለመሸጥ ከሆነ በፊደል ሠ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ከቆየበት ቦታ (ጋራዥ) ወይም ከቆመበት ቀበሌ አስተዳደር ማረጋገጫ ማስረጃ እስኪቀርብና እስኪረጋገጥ፣

ሰ. በትራንስፖርት ዘርፍ የተሰማራ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ ግብር ያልከፈለው የተሽከርካሪው ሊብሬ እና ታርጋ ለመንገድ ትራንስፖርት ስለመመለሱ ወይም መድን ድርጅት ቅሪት አካሉን ስለመረከቡ የሚያረጋግጥ ማስረጃ እስኪያቀርብ፣ወይም

ሸ. የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ተጠቃሚ የአገልግሎት ግዴታውን የተወጣ ስለመሆኑ የጽሑፍ ማስረጃ እስኪያሟላ ወይም የሚፈለግበትን ክፍያ እስኪፈጽም ድረስ፣

የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት መስጠት አይቻልም።

## ክፍል ሦስት

## የምስክር ወረቀት ለመስጠት በማጣራት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት እና አገልግሎቶች የሚስተናገዱበት አግባብ

### 6.የምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን የማጣራት ተግባር በማከናወን የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት አግባብ፤

ባለስልጣኑ ከላይ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸውን ሲያረጋግጥ በታክሱ አይነት ወይም በንግዱ ባህሪ፣ ወይም በስጋት ደረጃቸው፣ ወይም በሌሎች መረጃዎች ላይ በመመስረት በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሰረት አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ እና ቀጥሎ በተዘረዘረው አግባብ በማስተናገድ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት።



Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No.2

1.በክዋኔ ኦዲት ወይም በዴስክ ኦዲት ማጣራት የማያስፈልግ ሲሆን በደንበኞች አገልግሎት በቀጥታ በማስተናገድ ፤

2. በዴስክ ኦዲት ማጣራት ያለባቸውን በማጣራት በግብር አሰባሰብ የስራ ሂደት

3. በክዋኔ ኦዲት መጣራት ያለባቸውን በኦዲት አሰራር ድጋፍ የስራ ክፍሎች ተመርምሮ ኦዲቱ ሲጠናቀቅ በግብር አሰባሰብ የስራ ሂደት የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## 7. የኦዲት ክዋኔ ወይም የዴስክ ኦዲት የማያስፈልጋቸውና በደንበኞች አገልግሎት በቀጥታ የሚስተናገዱ አገልግሎቶች:-

የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ጠያቂዎች ከላይ በአንቀጽ 5(1) የተገለጹት ሁኔታዎች እስካሟሉ ድረስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የአገልግሎት አይነቶች ታክስ ከፋዩ ግለሰብ ነጋዴ ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ቢሆንም በኦዲት ክንዋኔ ወይም በስጋት ደረጃቸው ማጣራት ሳያስፈልግ በደንበኞች አገልግሎት በቀጥታ የሚስተናገዱ ይሆናል።

1.ንግድ ስራ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃድ ለማደስ፣

2. ጨረታ ለመካፈል/ ለመሳተፍ፤

3.ለተሽከርካሪዎች ወይም ለኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ /ክላውዶ/ ለማድረግ፣

4.ለተሽከርካሪ ቅሪት የመድን ካሳ ለማግኘትና የተሽከርካሪ ሰሌዳ ለውጥ ለማድረግ፣

5. የድርጅት ሥም ወይም አድራሻ ለመለወጥ፣

6. የንግድ ስራ ሀብት ቅነሳ የማይጨምር የንግድ ዘርፍ ቅነሳ፣

7.ከላይ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት የአገልግሎት አይነቶች በመሆናቸው ታክስ የማይከፈልባቸው ለመሆናቸው ማስረጃ የቀረበባቸውና በሚመለከተው አካል ተጣርተው የተረጋገጡ አገልግሎቶች፤

## 8. በግብር አሰባሰብ የስራ ሂደት የስራ ክፍሎች በዴስክ ኦዲት መጣራት ያለባቸው የአገልግሎት አይነቶች

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ... መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2 ... Revenues & Customs Authority ... Documentation No.2

ከላይ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ታክስ ከፋዩ በባለስልጣኑ የስጋት ስራ አመራር መርህ በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ስራ ሂደት በዴስክ ኦዲት መጣራት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች፤

1. **ታክስ ከፋዩ ግለሰብ ሆኖ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበትና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤**

ሀ. ከ 50% በታች የሆነውን የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፣

ለ. ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ግብር ስለመከፈሉ

ሐ..ይሁን እንጅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ግለሰብ ታክስ ከፋይ ዝቀተኛ የስጋት ደረጃ ያለው ቢሆንም ከ 50% በላይ የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም የንግድ ስራውን በከፊል ወይም በሙሉ ለመዝጋት የጠየቀ በሚሆንበት ጊዜ በክዋኔ ኦዲት መጣራት አለበት፡፡

2. **ታክስ ከፋዩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ**

ሀ. ከ 50% በታች የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፣

ለ. የንግድ ዘርፍንና ከ50% በታች የሆነ የንግድ ሀብት የሚቀንስ ከሆነ፣

ሐ.ህጋዊ ህልውና የነበራቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሀድ ዋናው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን አካቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የፀደቀ ሰነድ ከቀረበ፣

መ.ድርጅቱ የተቀጣሪዎቹን ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ግብር ስለመከፈሉና ለተቀጣሪ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ለማስጠት ቀጣሪ የስራ ግብር የተከፈለበት ስለመሆኑ ለታክስ ባለስልጣኑ ማረጋገጫ በጽሑፍ ከሰጠ፣

ሠ. ይሁን እንጅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ-መ) የተደነገገው ቢኖርም ታክስ ከፋዩ የህግ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያለው ቢሆንም ከ 50% በላይ የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም የንግድ ስራውን

Ethiopian Revenues & Customs Authority ... Documentation No.2

በከፊል ወይም በሙሉ ለመዝጋት የጠየቀ ሲሆን በክዋኔ ኦዲት መጣራት አለበት፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1 እና 2) የተገለፁት ታክስ ከፋዮች የንግድ ስራ ፈቃድ አውጥተው የንግድ ሥራ ያልሠሩ ከሆነ የንግድ ስራ ፈቃድ ለመመለስ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከባለስልጣኑ የስራ ክፍሎች እና ከሦሥተኛ ወገን በሚገኝ መረጃ መሰረት በዴስክ ኦዲት በማጣራት በታክስ አወሳሰን የስራ ሂደት በኩል የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚሰጥ ይሆናል፡፡
4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ቢሟሉም በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ(1-3) የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች የዴስክ ኦዲት ስራ እስኪጠናቀቅ ድረስ የምስክር ወረቀት አይሰጥም፡፡

9. **በታክስ ኦዲት ስራዎች ድጋፍ የስራ ክፍሎች በክዋኔ ኦዲት መጣራት ያለባቸው የአገልግሎት አይነቶች**

ከላይ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ ታክስ ከፋዩ በባለስልጣኑ የስጋት ስራ አመራር መርህ በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በክዋኔ ኦዲት መጣራት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች የምስክር ወረቀት ለመስጠት፤

1. **ታክስ ከፋዩ ግለሰብ ሆኖ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበትና መካከለኛ ወይም ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤**

ሀ. የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፤ወይም

ለ. ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ግብር ስለመከፈሉ፤ወይም

ሐ. በከፊልም ይሁን በሙሉ የንግድ ስራውን ለመዝጋት ሲጠይቅ የምስክር ወረቀት ከመስጠቱ በፊት በክዋኔ ኦዲት መጣራት ይኖርበታል፡፡

2. **ታክስ ከፋዩ ህጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት ሆኖ መካከለኛ ወይም ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤**

ሀ. ከ50 %( ሃምሳ በመቶ) በላይ የንግድ ስራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፤

ለ. ድርጅትን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመዝጋት፣

ሐ. የንግድ ስራ ሀብት መቀነስ፣ የሚጨምር እና ዘርፍ መቀነስ ከሆነ፣

መ. የንግድ መደብር ለሌላ አካል በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስ ወይም በመሳሰሉት ለማስተላለፍ፣

ሠ. ህጋዊ ህልውና የነበራቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሀድ ዋናው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን ሳያካትት ወይም አካቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የፀደቀ ሰነድ ከቀረበ፣

3. በፌደራል ገቢ ግብር አዋጁ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 42 መሠረት የግብር አወሳሰን ሊያደናቅፍ የሚችል ሁኔታ ኖሮ የታክስ ከፋዩ የባንክ ሂሣብ ከታገደና የፍርድ ቤት ትእዛዝ ወጥቶ የግብር አወሳሰኑ ካልተጠናቀቀ፣

4. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች ቢሟሉም በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1-3) የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች የዴስክ ኦዲት ስራ እስኪጠናቀቅ ድረስ ማንኛውም ታክስ ከፋይ የጠየቀውን የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም።

## 10. የባንክ ብድር ለማግኘት ለሚጠይቁ ታክስ ከፋዮች የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት አግባብ፤

በአዋጁ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ መሠረት …..ባንኮች ዋስትና የተቀበሉባቸው ሀብቶች ብድሩ ከመሰጠቱ በፊት ታክስ ከፋዩ የታክስ ዕዳ የሌለበት መሆኑን በባለስልጣኑ የተረጋገጠ ከሆነ ብቻ ነው"በማለት የተደነገገ በመሆኑ ባለስልጣኑ ከባንኮችና ከፋይናንስ ተቋማት ብድር ለማግኘት ለሚጠይቅ ማንኛውም ታክስ ከፋይ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው በሚከተለው አግባብ መሆን አለበት።

### 1. ባለስልጣኑ አገልግሎቱን የጠየቀው ማንኛውም ታክስ ከፋይ አስቀድሞ በንግድ ስራ የተሰማራ ሲሆን የምስክር ወረቀት ሲሰጥ፤

ሀ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ እና ለ) የተደነገጉት ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በተጨማሪ የታክስ ዕዳ የሌለበት ለመሆኑ በክዋኔ

ኦዲት ሲረጋገጥ በምስክር ወረቀቱ ላይ በግልጽ "ከማንኛውም የታክስ ዕዳ ነፃ ነው" በማለት መሆን አለበት፡፡

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ታክስ ከፋዩ በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ያለ ከሆነ እና በክዋኔ ኦዲት የታክስ ዕዳ እንዳለበት ሲረጋገጥ ባለስልጣኑ በሚሰጠው የምስክር ወረቀት ላይ በግልፅ "የታክስ እዳ ያለበት መሆኑን እና ባለስልጣኑ የቅድሚያ መብቱ በህግ የተከበረ ስለሆነ አበዳሪው አካል ይህንኑ ከግንዛቤ እንዲያስገባ እንገልፃለን" በማለት ገልፆ መሆን አለበት፡፡

ሐ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተዘረዘሩት ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ታክስ ከፋዩ በመካከለኛ ወይም በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያለ ከሆነ እና በክንዋኔ ኦዲት ተጣርቶ የታክስ እዳ ያለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ባለስልጣኑ በሚሰጠው የምስክር ወረቀት ላይ በግልፅ የስጋት ደረጃውን፤ የታክስ እዳ ያለበት መሆኑን እና ባለስልጣኑ የቅድሚያ መብቱ በህግ የተከበረ ስለሆነ አበዳሪው አካል ይህንኑ ከግንዛቤ እንዲያስገባ እንገልፃለን" በማለት ገልፆ መሆን አለበት፡፡

2. ባለስልጣኑ አገልግሎቱን የጠየቀው ማንኛውም ታክስ ከፋይ አስቀድሞ በንግድ ስራ ያልተሰማራ እና በግብር ዘመኑ አዲስ የተመዘገበ በሆነ ጊዜ ታክስ ከፋዩ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የፅሁፍ ማስረጃ ከሚኖርበት የቀበሌ ወይም የመስተዳድር አካል እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ ከባለስልጣኑ የመረጃ ቋት(ሲሰተም) አጣርቶ የምስክር ወረቀቱን በዚህ መመሪያ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

3. ከላይ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1(ሐ) የተደነገገው ቢኖርም ባለስልጣኑ በማጣራቱ ወቅት በመካከለኛ እና በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ያለ ታክስ ከፋይ የታክስ ዕዳ ያለበትና እዳውን ላይከፍል የሚችል መሆኑን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች መኖራቸውን ከተረዳ፤

ሀ. ታክስ ከፋዩ ፈቃደኛ ከሆነ የታክስ እዳውን ሊያካክስ የሚችል ንብረት እንዲያስይዝ በማድረግ እና ይሄው ንብረት ለሚመለከታቸው ንብረት መዝጋቢ አካላት በዋስትና እንዳይያዝ የእግድ ትዕዛዝ በመስጠት በሚሰጠው የምስክር ወረቀት ላይ ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1(ሐ) ከሚገለፀው በተጨማሪ ዕግዱን ገልፆ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ ወይም

ለ. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) መሰረት ታክስ ከፋዩ ለዕዳው ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት ለማስያዝ ፈቃደኛ ካልሆነ የማጣራቱ ስራ ሲጠናቀቅ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ ቁጥር 4 መሰረት በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ለታክስ ከፋዩ ምክንያቱን ጨምሮ የምስክር ወረቀት መስጠት እንደማይችል በጽሁፍ ምላሽ መስጠት አለበት።

4. ማንኛውም ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 (ለ ና ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው አግባብ በመግለጽ የምስክር ወረቀት ከሰጠ በኋላ ያበደረ ሲሆን የታክስ እዳን በተመለከተ በዋስትና በያዙት የታክስ ከፋዩ ሀብት ላይ ከባለስልጣኑ የቀደመ መብት አይኖራቸውም።
5. ማንኛውም ባንክ ወይም የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች መሰረት የምስክር ወረቀት የተሰጠውን ታክስ ከፋይ ንብረት በዋስትና በመያዙ የሚኖረው የቀደምትነት መብት በአዋጁ አንቀፅ 33 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) በተዘረዘሩት የታክስ አይነቶች ላይ እና በአዋጁ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀፅ 2 ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡
፡

## 11. በግብር ዘመኑ የስጋት ደረጃ ያልወጣላቸው አገልግሎት ጠያቂዎች በተመለከተ

1. የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ለዚህ መመሪያ ክፍል 3 ድንጋጌዎች አፈፃፀም ሲባል አገልግሎት የጠየቀው ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ የስጋት ደረጃ ያልወጣለት ከሆነ የባለስልጣኑ የስጋት ስራ አመራር ዳሬክቶሬት ወይም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የስጋት ስራ አመራር ቡድን የስጋት ደረጃ እንዲያወጣላቸው ተደርጎ የማጣራት ስራ መስራት አለበት።
2. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተሰራው የስጋት ደረጃቸው ከፍተኛ የሆኑትን ታክስ ከፋዮች መረጃ ለኦዲት አሰራርና ድጋፍ እና ለስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በየወሩ ይልካሉ።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 12. የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚያገለግልበት ጊዜ ገደብ

1. በጨረታ ለመሳተፍ ወይም ከባንክ የብድር አገልግሎት ለማግኘት ከሆነ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ 6 ወር ድረስ ብቻ፤
2. የንግድ ፈቃድ ለማሳደስ፣ተሽከርካሪን ለማስፈተሽ(ካላዉዶ ለማስደረግ) የሚሰጥ የታክስ ምስክር ወረቀት ከሆነ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለተጻፈበት የግብር ዘመን ብቻ ሆኖ፡-

   ሀ.በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ሂሳባቸውን ለሚዘጉ እስከ ሰኔ 30 ድረስ፣

   ለ.ሂሳባቸውን በራሳቸው የሂሳብ ጊዜ ለሚዘጉ የሂሳብ ጊዜያቸው ማጠናቀቂያ ቀን ድረስ ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡
3. የንግድ ስራቸውን በከፊል ወይም በሙሉ ለማቋረጥ፣ የባለቤትነት ስም ለውጥ ለማድረግ ወይም የንግድ ሀብትን ለማስተላለፍ የሚሰጥ ከሆነ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሦስት ወራት ብቻ፣
4. የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ክፍያን በአገልግሎት ወይም ገንዘብ በመክፈል ግዴታውን የተወጣ ተጠቃሚ የሚሰጠዉ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የትምህርት ማስረጃውን ለመቀበል ብቻ የሚያገለግል ይሆናል፡፡
5. ለዚህ አንቀጽ አፈጻፀም ሲሆን የአገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ የሚያገለግሉ ቅጾችን ያዘጋጃል፡፡

### 13. ለታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አገልግሎት ጥያቄ በባለስልጣኑ ምላሽ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ፤

የታክስ ባለሥልጣኑ፡-

1. ታክስ ከፋዩ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን ማሟላቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና 2 ድንጋጌዎች መሠረት የክዋኔ ኦዲት ወይም የታክስ ኦዲት ማድረግ ሳያስፈልጋቸው ለደንበኞች

Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No.2

አገልግሎት በቀጥታ የሚስተናገዱ ታክስ ከፋዮችን በተመለከተ ለታክስ ከፋዩ ማመልከቻውን ባቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ድንጋጌ መሠረት የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ለመስጠት በዴስክ ኦዲት መጣራት ያለባቸው እና በግብር አሰባሰብ የስራ ሂደት የሚስተናገዱ ታክስ ከፋዮችን በተመለከተ የዴስክ ኦዲት ስራው ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ ባሉት 14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 እና አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ እና ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች መሠረት የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ለመስጠት በክዋኔ ኦዲት መጣራት ያለባቸው እና በግብር አሰባሰብ የስራ ሂደት የሚስተናገዱ ታክስ ከፋዮችን በተመለከተ የክዋኔ ኦዲት ስራው ከተጠናቀቀበት ቀን አንስቶ ባሉት 14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ሁኔታ የክዋኔ ኦዲት ስራው በዘጠና ቀናት ውስጥ መጠናቀቅና ከዚህ ቀን አንስቶ በሚቆጠር ባሉት 14 ቀናት ውስጥ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1-3) የተደነገገው ቢኖርም ባለስልጣኑ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት የማይቻልበት ምክንያት ያለ መሆኑን ሲያምንበት የምስክር ወረቀት መስጠት ባለበት ቀናት ውስጥ የማይሰጥበትን ምክንያት ለታክስ ከፋዩ በጽሁፍ መልስ መስጠት አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1-4) በተገለጸው ጊዜ ውስጥ የታክስ ክሊራንስ ለጠየቀ ሰው በጽሁፍ ምላሽ ያልሰጠ የባለስልጣኑ ሰራተኛም ሆነ ኃላፊ ቅሬታ ሲቀርብበት ባሉት የሰራተኛ አስተዳደር ህጎች ተጠያቂ ይሆናል ፡፡

## 14. ቅሬታ ስለማቅረብ

ከታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በባለስልጣኑ አሰራር ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለቅ/ጽ/ቤቱ ቅሬታ ሰሚ ስራ ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡

## 15. የተሻረ መመሪያ

1. የግብር ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት(ክሊራንስ) አሰጣጥ በተመለከተ በመመሪያ ቁጥር 55/2003 የተደነገገው የመመሪያው ክፍል በዚህ መመሪያ ተሽሯል
2. በታክስ ክሊራንስ ጥያቄ በቅድሚያ ኦዲት መደረግ ያለባቸውና የሌለባቸው ግብር ከፋዮችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 128/2009 በዚህ መመሪያ ተሽሯል።
3. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሰርኩላር ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡

## 16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በነዚሁ በቀድሞ መመሪዎች መሰረት ፍጻሜ ያገኛሉ።

## 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ሆናል።

አዲስ አበባ

2010 ዓ.ም

**ዑመር ሁሴን**
**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር(ሚኒስትር)**

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ሬ.ዶ መዝገብና ዶክመንቴሽን ቁ.2
15
Ethiopian Revenues & Customs Authority
Records & Documentation No.2